**2023-2024 የታቀደው የሁለት ዓመት አጋማሽ የበጀት ማስተካከያዎች**

ይህ በጀት የከንቲባ ብሩስ ሃረልን ቀጣይ ቁርጠኝነት እና የማህበረሰቦቻችንን ፍላጎት በሚያሟሉ ተግባራት ላይ መዋዕለ ንዋይ ማፍሰስን እና የ***One Seattle*** ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ነገሮች ያንፀባርቃል። የከንቲባው ሃሳብ ደህንነቱ የተጠበቀ እና ጤናማ ማህበረሰቦችን ለመፍጠር መዋዕለ ነዋይ ፈሰስ ማድረጉን ቀጥሏል። ይህ በጀት የህዝብን ደህንነት ለማረጋገጥ፣ ተመጣጣኝ መኖሪያ ቤት ለመገንባት፣ የቤት እጦትን ችግር ለመፍታት እና የመሀል ከተማችንን ነዋሪዎች፣ ሰራተኞች፣ ጎብኝዎች ጊዜ ለማሳለፍ እና ለሁሉም እድል እና ፍትሃዊነትን ለማጎልበት የሚካሄዱ ጥረቶችን ይደግፋል።

ለሥነ ጥበብ እና ባህል ቢሮ፣ የታቀደው በጀት የሚከተሉትን ያጠቃልላል:-

- $1,000,000 የ Hope Corps የድጋፍ ፕሮግራምን፡ (ከሚገባቸው በታች በሆነ ስራ ላይ ያሉ እና ሥራ አጥ የሆኑ አርቲስቶችን ከሙያ ዕድገት እድሎች ጋር የሚያገናኝ ፕሮግራም) ዳውንታውን ላይ በማተኮር እስከ 2024 ድረስ ለማስቀጠል።
- $1,000,000 ከ Office of Economic Development (ኢኮኖሚ ልማት ጽህፈት ቤት) ጋር በመተባበር የፈጠራ ኢኮኖሚን ለመደገፍ እና የኪንግ ስትሪት ጣቢያን እና በዙሪያው የሚገኙ የመሀል ከተማ ሰፈሮችን ለማነቃቃት።
- በአንድ ግዜ ድጋፍ መልክ የሚሰጥ $650,000፡ ከወረርሽኙ በማገገም ላይ የሚገኙ የጥበብ እና የባህል ድርጅቶችን ለመደገፍ የሚውል።
- $257,100፡ በቀጣይነት የሚሰጥ ግራንት ማስተካከያ፡ የቅርብ ጊዜውን የዋጋ ግሽበት ለመቅረፍ የሚውል።

በታቀደው በጀት ላይ ለበለጠ መረጃ፣የከንቲባውን ጋዜጣዊ መግለጫ እዚህ ያንብቡ፡ [Mayor Harrell Announces 2024 Budget Proposal – Office of the Mayor] (በእንግሊዘኛ ቋንቋ)